# የርስዎ መረጃ ግላዊ ነው

## በዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆኑ መረጃው ምን ይደረጋል?

### እኛ ማን ነን?

ከአካባቢ ብዛት ካለው የማህበራዊ እንክብካቤ እና የጤና ጥበቃ አገልግሎት ውስጥ አንደኛው ስንሆን ሁሉም በአንድነት በመሆን የርስዎን ጤና ጥበቃ ፍላጎት ለማሟላት ድርሻ ይኖረዋል።

### ስለርስዎ ምን ዓይነት መረጃ ነው የምንሰበስበው?

በተገልጋይ መዝገብ ላይ የርስዎን ስምና አድራሻ ዝርዝር እናስቀምጣለን። ሌሎች ዝርዝር መረጃ ማለት እንደ ስለርስዎ ጤና ጥበቃ እቅድ አወጣጥና የመረጃ ሪፖርት በየጊዜ ሲሄዱ ይመዘገባል።

### ለምንድነው መረጃ የምንሰበስበው?

ስለሚያስፈልግዎ እርዳታ ለማወቅ የምንሰበስበው መረጃ ሲረዳን ታዲያ በተቻለው መንገድ እንክብካቤ ልናቀርብልዎት እንችላለን። እንዲሁም የተሻለ አገልግሎት ለማካሄድና እቅድ ለማውጣት ይህንን መረጃ እንጠቀማለን።

### የርስዎን መረጃ ሌላ ሰው ማን ያየዋል?

የርስዎ መረጃ በርስዎ እንክብካቤ ተሳትፎ ላደረገ ባለሙያ ብቻ ሊያየው ይችላል። ከዚህ ባሻገር በህግ በተደነገገው መሰረትና ከተስማሙ ስለ ርስዎ መረጃ በድንገተኛ ህክምና ጊዜ ይሰጣል።

### በቀረበው መረጃዎ ላይ ምን አስተያየት አለዎ?

ያቀረቡት መረጃ ምን ደረጃ እንደደረሰ ለማወቅ መብትዎ ነው። ባቀረቡት መረጃ ተመርኩዘን ትክክለኛ የሆነ እንክብካቤ እናደርግልዎታለን። አንዳንድ መረጃዎችን ለእኛ ማካፈል ካልፈለጉ ወይም ለተወሰነ መረጃ ብቻ ለማነጋገር ከፈለጉ መብትዎ ነው። ነገር ግን ለምናቀርብልዎ አገልግሎት ጥሩ ላይሆን ይችላል። ባልተስማሙበት ጉዳይ ላይ ለማሰረዝ ከፈለጉ ያነጋግሩን።

### ያቀረቡት መረጃ እንዴት ይጠበቃል?

የርስዎን መዝገብ በሚስጢር እንደሚጠበቅ ልናረጋግጥልዎ እንፈልጋለን። የርስዎ ግላዊ መረጃ በሚስጢር መያዙ በህግ የተደገፈ ነው። የርስዎን ግላዊ የሆነ መረጃ በሚስጢር ለመያዝና በጥሩ ቦታ ላይ ይቀመጣል።

### የርስዎን መረጃ ማግኘት ይችላሉን?

አወ፡ ስለርስዎ ግላዊ መረጃ ለመጠበቅ መብትዎ ሲሆን እንዲሁም ስህተት ካለ እርምት እንዲደረግበት መጠየቅ እንደሚቻል ነው።

### ሌላ ጥያቄዎች ካለዎት?

የእኛን አገልግሎት በሚቀርብልዎ ጊዜ ስለሰጡት መረጃ ምን እንደተደረገ የሆነ መረጃ ወይም ቅሬታ ካለዎት ወይም የርስዎን መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ እባክዎ ለጽህፈት ቤቱ አንደኛው ሠራተኛ ያነጋግሩ።

The Department of Human Services, 2009

Victoria
The Place To Be